# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ

0

## በደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ለተደራጁ ማህበራት ማበረታቻ አከፋፈል መመሪያ




ግንቦት/2013 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ማበረታቻ የአፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 96/2014

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ በከተማው የሚመነጨው ደረቅ ቆሻሻ በአግባቡ ተለይቶ ጥቅም ላይ ለማዋል የደረቅ ቆሻሻ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላትን እንደገና ለማደራጀት፤ ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 64/2011 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (3) ተራ ፊደል (ሠ) መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳዳር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳዳር ኤጀንሲ የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ማበረታቻ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 96/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል

### 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃላት አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጣቸው በቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. *"ኤጀንሲ"* ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
2. *"ማህበር"* ማለት የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስበው ለመሸጥ በህጋዊ መንገድ የተደራጁ ወይም ከደረቅ ቆሻሻ ኮምፖስት አምርተው ለመሸጥ በህጋዊ መንገድ የተደራጀ ማህበራት ነው፤
3. *"ማበረታቻ"* ማለት ወረቀትና ካርቶን ሰብስበው ለሚሸጡ ወይም ኮምፖስት አምርቶ ለሚሸጥ ማህበራት በሸጠው የኮምፖስትና ወረቀት መጠን በኤጀንሲው በሚወስነው ታሪፍ መሰረት በኪሎ ግራም ወይም በሜትር ኩብ እየተሰላ የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራን ለማበረታታት ለማህበሩ የሚከፈል ክፍያ ነው፤

4. ***"ጽህፈት ቤት"*** ማለት በክፍለ ከተማ ወይም በወረዳ ደረጃ እንደአግባብነቱ ያለ የስራ እድል ፈጠራና ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ነው፤

**3. የመመሪያው ተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ የወረቀት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስበው በሚሸጡ ህጋዊ ማህበራት እና ኮምፖስት አምርተው በሚሸጡ ህጋዊ ማህበራት ላይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

### <u>ማበረታቻ የሚሰጣቸው የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ማህበራት</u>

**4. ማበረታቻ የሚሰጣቸው የደረቅ ቆሻሻ መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች**

1. ለመልሶ መጠቀምና ኡደት አገልግሎት ተሰብስቦ የተሸጠ የወረቀትና ካርቶን ደረቅ ቆሻሻ እና ከሚበሰብስ ደረቅ ቆሻሻ ተመረቶ የተሸጠ ኮምፖስት ብቻ ማበረታቻ የሚሰጣቸው የመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ስራዎች ናቸው፤

2. ከመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ውጭ የተደራጀ ማንኛውም ማህበር ወይም ግለሰብ የኮምፖስትም ይሁን የወረቀትና ካርቶን ማበረታቻ ክፍያ አይሰጠውም፤

**5. ማበረታቻ ስለሚደረግለት ማህበር**

1. የወረቀትና ካርቶን ድጎማ የሚከፈለው ማንኛውም ማህበር በወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት በኩል በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ማህበሩ እንዲደራጅ ለስራ እድል ፈጠራ ጥያቄ ቀርቦ ማህበሩም በስራ እድል ፈጠራ በኩል በህጋዊ መንገድ የተደራጀ ሊሆን ይገባዋል፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ በህጋዊ መንገድ የተደራጀው ማህበር የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት እንዲሁም የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ እንዲያውቁትና እንዲመዘግቡት ካልተደረገ በስተቀር ማበረታቻው ሊከፈለው አይችልም፤

## 6. ስለ ስራ ውል ስምምነት

1. የኮምፖስት ማበረታቻ የሚከፈለው ማንኛውም ማህበር በወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት በኩል በኮምፖስት መልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ማህበሩ እንዲደራጅ ለስራ እድል ፈጠራ ጥያቄ ቀርቦ ማህበሩም በጽህፈት ቤቱ በኩል በህጋዊ መንገድ የተደራጀና የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት እንዲሁም ኤጀንሲው የሚያውቁትና የመዘገቡት ማህበር ብቻ ነው፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ማህበር የወረቀት፣ ካርቶንና የኮምፖስት ማበረታቻ ለማግኘት የተደራጀበትን ህጋዊ ሰነድ በማያያዝ ከወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ጋር የስራ ውል ስምምነት ሊኖረው ይገባል፤

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለ ማበረታቻ አቀራረብና አወሳሰን</u>

## 7. የወረቀት፣ ካርቶንና ኮምፖስት ማበረታቻ ለመጠየቅ የሚያስፈልግ መረጃ

1. ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ተደራጅቶ ከወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ጋር ህጋዊ ውል የተዋዋለ ማህበር የወረቀት፣ ካርቶን ወይም የኮምፖስት ማበረታቻ ሲጠይቅ በህጋዊ ማህበሩ ደብዳቤ ምን ያክል ግብዓት እንደሸጠ በሜትር ኩብ ወይም በኪሎ ግራም ገልጾ ጥያቄውን ለወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ የተደራጀ ማህበር የወረቀት፣ ካርቶንና የኮምፖስት ማበረታቻ ለወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት በደብዳቤ ሲያስገባ ግብዓቱን የሸጠበትን ደረሰኝ አያይዞ የማቅረብ ግዴታ አለበት፤

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የወረቀት፣ ካርቶንና የኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ የሚጠይቅ ማህበር የራሱን የሽያጭ ደረሰኝ ለማበረታቻ ክፍያ ሲያቀርብ ግዥ የፈጸመው ተቋም፣ ድርጅት

ወይም ማህበር ግዥ ለመፈጸሙ ጥያቄ ያቀረበበት ወይም የገዛበት የኮምፖስት ወይም የወረቀት መጠን የተገለጸበት ህጋዊ ቁጥርና ማህተም ያለው ደብዳቤ አያይዞ ማቀረብ አለበት፤

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረቀት ደረቅ ቆሻሻን ከመልሶ መጠቀምና ኡደት ማድረግ ማህበራት ግዥ የፈጸመ ደርጅት ግዥ ለመፈጸሙ ደረሰኝ ለማህበሩ የሚሰጠው ከሆነ ማህበሩ ግዥ በፈጸመለት ድርጅት ደረሰኝ ማበረታቻ መጠየቅ ይችላል፡፡ ነገር ግን ለማበረታቻ የሚቀርበው ደረሰኝ በገቢዎች ቦሮ ፈቃድ የታተመ ደረሰኝ ሆኖ ደረሰኝ ቁጥርና የድርጅቱ ስምና አርማ ከላይ ያረፈበት ሊሆን ይገባል፤

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የወረዳው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ማህበሩ የጠየቀውን የወረቀት፤ ካርቶንና ኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ በማጣራትና በማረጋገጥ እንዲሁም የሽያጭ ሰነዶችንም በማያያዝ ማበረታቻው እንዲከፈላቸው ለክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት በደብዳቤ ያሳውቃል፤

8. የወረቀት፤ ካርቶንና የኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ አሰጣጥና መጠን

1. የክፍለ ከተማው ዋና ስራ አስኪያጅ ጽህፈት ቤት ከወረዳ የመጣለትን የወረቀት፤ ካርቶንና ኮምፖስት ማበረታቻ የክፍያ ሰነድ በማረጋገጥና በማጣራት ክፍያ እንዲፈጸም ያደርጋል፤

2. የኮምፖስት፤ የወረቀትና ካርቶን ማበረታቻ ክፍያ የሚፈጸመው በአዲስ ብድርና ቁጠባ ተቋም በኩል ነው፤

3. የወረቀት፤ ካርቶንና ኮምፖስት ማበረታቻ ክፍያ ከአቅም በላይ የሆኑ ችግሮች ካልተፈጠሩ በቀር በየወሩ መጨረሻ ከቀን 25-30 ባሉት ቀናት ተጣርቶና ተረጋግጦ ለማህበሩ ክፍያ ይፈጸማል፤

4. አሁን ባለው ዋጋ ለአንድ ኪሎ ግራም ኮምፖስት ማበረታቻ ብር 3.00 (ሶስት ብር) ወይም አንድ ሜትር ኩብ ኮምፖስት ማበረታቻ ብር 800.00 (ስምንት መቶ ብር)

እንዲሁም አንድ ኪሎ ግራም ወረቀት ማበረታቻ ብር 1.50 (አንድ ብር ከሃምሳ ሳንቲም) ይከፈላል፤

5. ኤጀንሲው ለኮምፖስት፣ ወረቀትና ካርቶን ማበረታቻ ክፍያ እንደ ሁኔታው ዋጋውን ከፋይናንስ ቢሮ ጋር በመነጋገር ሊያሻሽል፣ ሊያቆም ወይም ሊያራዝም ይችላል፤

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን መመሪያ በማስፈፀም ረገድ በዚህ መመሪያ ከተጠቀሱት አካላት ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 10. መመሪያውን ስለማሻሻል

- ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 11. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮችና መመሪያዎች

- ከዚህ መመሪያ ውጭ ያሉ መመሪያዎችና የውስጥ አሰራሮች በዚህ መመሪያ በተሸፈኑ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### ፲፪. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

- ይህ መመሪያ ከዛሬ ከግንቦት 01 /2013 ዓ፣ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ኤጀንሲ**

# The Addis Ababa City Government

# Solid Waste Management Agency

## An Incentive Payment Directive for Associations Engaged in the Reusing and Recycling of Solid Wastes

**May 2021,**

**Addis Ababa**

# The Addis Ababa City Government Solid Waste Management Agency Solid Waste reusing and recycling Activities Incentive Implementation Directive Number 96/2021

**WHEREAS,** it has been found necessary to encourage solid waste reusing and recycling activities in order to properly sort out the solid wastes generated in the city and utilize it accordingly;

**NOW, THEREFORE,** in accordance with letter (e) of Sub-Article (3) of Article 15 of the Addis Ababa City Government Executive Organs Re-establishment and to Specify the Power and Duties of the thereof Proclamation No. 64/2019 (as amended), the Addis Ababa City Government Solid Waste Management Agency has issued this directive.

## PART ONE

## GENERAL PROVISIONS

1. **Title**
   This directive may be cited as: **"The Addis Ababa City Government Solid Waste Management Agency Solid Waste Reusing and Recycling Activities Incentive Implementation directive no. 96/2021."**

2. **Definition**
   In this directive, unless the context requires otherwise:
   1. **"Agency"** means the Addis Ababa City Solid Waste Management Agency;
   2. **"Association"** means associations that are legally organized to collect and sell paper solid wastes or those associations that are legally organized to produce compost from solid wastes;
   3. **"Incentive"** means an incentive payment for an association, to encourage reusing or recycling of solid wastes, based on the tariff specified by the agency, either in kilograms or cubic meter, for those associations that collect and sell papers and carton or to those that produce and sell compost as per the amount of the compost and paper it sell;
   4. **"Office"** means the job opportunities creation and enterprise development office that exists at the sub-city or *'woreda'* level.

3. **Application Scope of the Directive**
   The directive shall only be applicable on those legitimate associations that collect and sell paper solid wastes and on those lawful associations that produce and sell compost.

## PART TWO

## ASSOCIATIONS ENGAGED IN REUSING AND RECYCLING ACTIVITIES THAT RECEIVE INCENTIVES

4. **Solid Waste Reusing and Recycling Activities that receive Incentives**

   1. Solid waste papers and carton that are collected and sold for the purpose of reusing and recycling and compost produced from decayable solid waste and sold are the only reusing and recycling activities that receive incentives.

   2. Any individual or any association established out of the reusing and recycling service will not get a compost or paper and carton incentive payment.

5. **Associations entitled to Incentives**

   1. Any association subsidized for carton and paper should be legally organized by the job creation and enterprise development office through a request submitted by the general manager office of the *'woreda'* to the thereof that the association is going to be engaged in the reusing and recycling service.

   2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, the legally organized association will not receive the incentive payment unless its establishment is recognized and registered by the general manager office of the sub-city and by the solid waste management agency.

6. **Business Agreement**

   1. Any association that receive an incentive for compost production should be legally organized by the job creation and enterprise development office through a request submitted by the general manager office of the *'woreda'* to the thereof that the association is going to be engaged in compost reusing and recycling service as well as it should only be recognized and registered by the general manager office of the sub-city and the agency.

   2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, any association should have a business agreement with the general manager office of the *'woreda'*, by attaching its establishment document, to get the paper, carton and compost incentive.

## PART THREE

## REQUEST FOR INCENTIVE AND DECISION MAKING

### 7. Evidences Needed for the Request of Paper, Carton and Compost Incentive

1. Any association organized in the reusing and recycling service and enter into a business agreement with the general manager office of the *'woreda'*, that asks for paper, carton, or compost incentive, shall be obliged to state the amount of its sell in cubic meter or kilograms in its formal letter and submit same to the general manager office of the *'woreda'*.

2. Without prejudice to Sub-Article (1) of this Article, any association organized in the reusing and recycling service, while requesting paper, carton, and compost incentive, to the general manager office of the *'woreda'* in its formal letter, is obliged to attach the receipt for selling the input.

3. Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, any association that requests paper, carton, and compost incentive payment, while submitting its own sells voucher, it must also present the formal letter of an institution, organization or association that states a request for transaction or the amount of compost or paper it has purchased.

4. Without prejudice to Sub-Article (3) of this Article, an association engaged in the paper solid waste reusing and recycling service can request the incentive payment using the receipt of an organization that purchases the product if the organization gives a receipt for the association that corroborate the transaction. However, the receipt should be produced under the permission of the Revenue Bureau and should have serial number and consist the name and emblem of the organization.

5. Without prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the general manager office of the *'woreda'* shall examine and verify the paper, carton, and compost incentive payment as well as attach the transaction documents; and notify same to the general manager office of the sub-city through a formal letter to complete the payment.

### 8. Paper, Carton and Compost Incentive Payment Delivery and Amount

1. The general manager office of the sub-city shall verify and examine the paper, carton, and compost incentive payment documents sent by the *'woreda'* and cause payments to be completed.

2. The compost, paper, and carton incentive payment shall be carried out through Addis loan and savings Institution.

3. The paper, carton, and compost incentive payment shall be examined, and verified as well as will be paid to the association at the end of every month between the 25th to the 30th days of the month.

4. With the current price, an incentive of birr 3.00 (Three birr) shall be paid for one kilogram of compost or an incentive of birr 800.00 (Eight hundred birr) shall be paid for one cubic meter compost as well as birr 1.50 (One birr and fifty cents) shall be paid for one kilogram of paper.

5. The agency may, as per conditions, improve, hold or extend the compost, paper, and carton incentive payment in consultation with the Finance Bureau.

## PART FOUR

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

### 9. Duty to Cooperate

Any person shall be duty bound to cooperate with the indicated organs in this directive regarding its implementation.

### 10. Amending the Directive

The Agency may amend this directive as it is found necessary.

### 11. Inapplicable Procedures and Directives

Any directives and internal procedures which are inconsistent with this directive shall have no effect.

### 12. Effective Date

This directive shall enter into force as of this 9th day of May, 2021.

**The Addis Ababa City Government**

**Solid Waste Management Agency**